# መመሪያ ቁጥር 154/2016

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ የንግድ ትርዒትና ባዛር መመሪያ

**አዲስ አበባ**

# መመሪያ ቁጥር 154/2016

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ የንግድ ትርዒትና ባዛር መመሪያ

የንግድ ትርዒትና ባዛር አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል የንግድና የመዋዕለ ነዋይ ፍሰት፣ የንግድ ውድድር እየጨመረ በመምጣቱ፤ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እየወጣባቸው ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡትን ምርቶች በሃገር ውስጥ ምርቶች በመተካት የውጭ ምንዛሬ ለመቀነስ እንዲቻል፤ በአምራቾች፣ አገልግሎት ሰጭዎችና ተጠቃሚዎች መካከል በጋራ ጥቅሞቻቸው ላይ የተመሠረተ የንግድ ልውውጥ ጤናማ የንግድ ግንኙነት በአግባቡ ለመምራት ወቅቱ በፈጠራቸው ሳይንስና ቴክኖሎጂ የተመረቱትን ምርቶች ለማስተዋወቅና የሸማቹን ፍላጎትና የመግዛት አቅም ባገናዘበ መልኩ የንግድ ሥርዓቱን በህግ አግባብ መምራት በከተማችን የንግድ ትርዒትና ባዛር ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ይታወቃል፡፡

በዚህ መሠረት በንግድ ትርዒትና ባዛር ፈቃድ አሰጣጥና አፈጻጸም ዙሪያ እየታዩ ያሉትን ችግሮች ለማስወገድ እና በተገቢው መንገድ ለመምራት እንዲቻል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 16 (2) (ሠ) እና 31(2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የንግድ ትርዒትና ባዛር መመሪያ ቁጥር 154/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር

1. "**ቢሮ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ማለት ነው፡፡
2. "**ባዛር**" ማለት ንግድን ለማስፋፋት ሲባል የቴክኖሎጂ ግኝቶችን፣ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርት ውጤቶችን፣ የዕደ ጥበብ ውጤቶችን፣ አገልግሎትን ለማስተዋወቅ በአካል ፣ወይም በፎቶ ግራፍ ወይም በመረጃ ቴክኖሎጂና በተለያዩ መንገዶች በዚህ መመሪያ አንቀፅ 3 ሥር ከተጠቀሱት ቢያንስ አንዱን ዓላማ ይዞ ለህዝብ እይታ በማቅረብ እያስተዋወቁ መሸጥ ነው፡፡
3. "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
4. "**አዋጅ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ለቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 84/2016 ነው፡፡
5. "**የሀገር ውስጥ ንግድ ትርዒት**" ማለት በሀገር ውስጥ አምራች፣አስመጪ ወይም በንግድና ኢንዱስትሪ ነክ የሙያ ማህበራት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚዘጋጅ የንግድ ትርዒት ነው፡፡
6. "**የንግድ ትርዒት**" ማለት ንግድን ለማስፋፋት ሲባል የቴክኖሎጂ ግኝቶችን፣ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርት ውጤቶችን፣ የዕደ-ጥበብ ውጤቶችን እና አገልግሎትን ለማስተዋወቅ በአካል ወይም በፎቶ ግራፍ ወይም በመረጃ ቴክኖሎጂና በተለያዩ መንገዶች በዚህ መመሪያ አንቀፅ 3 ሥር ከተጠቀሱት ቢያንስ አንዱን ዓላማ ይዞ ለህዝብ የሚታይበት መድረክ ወይም ኤግዚቢሽን ወይም አውደ ራዕይ ነው፡፡
7. "**ፈቃድ**" ማለት የንግድ ትርዒት ወይም ባዛር ወይም የንግድ ትርኢትና ባዛር ለማካሄድ በንግድ ቢሮ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

## 3. የሀገር ውስጥ ንግድ ትርዒት (ኤግዚቢሽን) እና ባዛር ዓላማዎች

የሀገር ውስጥ ንግድ ትርዒት (ኤግዚቢሽን) የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1. ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውሉና ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ የሃገር ውስጥ ምርቶችና አገልግሎቶችን በንግድ ህግና ሥርዓት ለማስተዋወቅ፤
2. በአምራች፣ አገልግሎት ሰጪዎችና ተጠቃሚዎች መካከል በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ የንግድ ልውውጥና ግንኙነት በመፍጠር የገበያ አድማስ ለማስፋት፤
3. ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝምና ለኢንቨስትመንት ያለውን ምቹ ሁኔታ፣ ግኝቶችና እድሎች በማስተዋወቅ እድገትና ልማትን ለማበረታታት፤
4. በአምራቾችና አገልግሎት ሰጪዎች መካከል አግባብነት ያለው ውድድር ለማስፈን እና የልምድ ልውውጥ እንዲኖር ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፤
5. በአምራቹና በሸማቹ ህብረተሰብ መካከል ያለውን የገበያ ሰንሰለት በማሳጠር ለሸማቹ ህብረተሰብ የገበያ አማራጭ ለመፍጠር፤
6. በሀገር ውስጥ የተመረቱና ከውጭ ሀገር የገቡ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ አዳዲስ ግኝቶችና የፈጠራ ሥራዎች እንዲተዋወቁ በማድረግ ለተስማሚ ቴክኖሎጂ መረጣ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ለአገሪቱ ልማት እንዲውል ለማስቻል እንዲሁም
7. ሌሎች ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ዓላማዎች ጋር ተዛማጅነትና ተመሳሳይነት ያላቸው ተግባራትን ለማሳካት፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚዘጋጅ የንግድ ትርዒት ወይም ባዛር ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት እና ስለፍቃድ አሰጣጥ

## 5. የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት

1. ከተማ አቀፍ የንግድ ትርዒት፣ ባዛር፣ የንግድ ትርዒትና ባዛር መዝገብ ያቋቁማል፤ ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፡፡

2. የንግድ ትርዒት፣ ባዛር፣ የንግድ ትርዒትና ባዛር ይመዘግባል፡፡
3. በከተማ ውስጥ ለሚካሄድ የንግድ ትርዒት፣ ባዛር፣ የንግድ ትርዒትና ባዛር ፈቃድ ይሰጣል፡፡
4. ለሚመለከታቸው አካላት እና ጥያቄ ለሚያቀርቡ ሰዎች እንደአስፈላጊነቱ የንግድ ትርዒትና ባዛር መረጃዎችን ይሰጣል፡፡
5. የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልጋቸውን የንግድ ትርዒት፣ ባዛር፣ የንግድ ትርዒትና ባዛር ላይ የሚቀርቡ ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ እንደ አግባቡ ከሚመለከታቸው የሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን ይለያል፤ መስፈርቶች እንዲዘጋጅላቸው እና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጥም ያስተባብራል፡፡
6. ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት እንደአግባቡ የንግድ ትርዒት፣ ባዛር ወይም የንግድ ትርኢትና ባዛር የሚካሄድባቸውን ቦታዎች፣ መንገዶች፣ አደባባዮች ከሚያስተዳድረው እና ከሚቆጣጠረው ከትራፊክ ማኔጅመኔት ኤጀንሲ የተሰጠ ፈቃድ መኖሩን ያረጋግጣል፡፡
7. ፈቃድ በሰጠባቸው ተግባራት መሠረት በትክክል እየተካሄደ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
8. በንግድ ትርዒት፣ ባዛር ወይም ንግድ ትርዒትና ባዛር ላይ ለሚሳተፉ አካላት የአቅም ግንባታ እና አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ድጋፎችን ይሰጣል፡፡
9. በዚህ መመሪያ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን የሚከታተሉ ተቆጣጣሪዎችን ይመድባል፡፡

## 6. ፈቃድ ስለማውጣት

1. ማንኛውም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ትርዒት፣ ባዛር ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛር ማካሄድ አይችልም፡፡
2. በኤግዚቢሽን ማእከል እና የገበያ ልማት ድርጅት ከሚካሄድ ዝግጅት ውጭ ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት የንግድ ትርዒት፣ ባዛር ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛር ለማካሄድ በቢሮው የተፈቀደበትን ደብዳቤ መያዝ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከተፈቀደለት ውጭ ምንም አይነት ሌላ ተግባር ማካሄድ በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡
4. የተፈቀደለት ሰው ማካሄድ የሚችለው በተፈቀደለት ቀናት ብቻ ነው፡፡

5. የንግድ ትርዒት፣ ባዛር ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛር የተፈቀደለት ማንኛውም ሠው በቢሮው በተሰጠው የሪፖርት ቅጽ መሠረት የተፈቀደለት ቀን ካበቃ ቀን ጀምሮ ባሉት ሠባት ቀናት ጊዜ ውስጥ የተካሄደውን ዝግጅት የሚመለከት ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

## 7. ፈቃድ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው መረጃዎች

1. ለዚህ አላማ ቢሮው ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት አስፈላጊ ሰነዶችን በማያያዝ ፈቃድ እንዲሰጠው ለቢሮው ማመልከት ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ጥያቄ አቅራቢው ***የንግድ ድርጅት*** ከሆነ

ሀ) የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ኮፒ፤ በውክልና ከሆነ ህጋዊ የውክልና ማስረጃና የአመልካቹ የታደሰ መታዎቂያ፤

ለ) ልዩ ዝግጅት የማስተባበር ወይም ኤቨንት ኦርጋናይዘር(አስተባባሪ) ወይም የማስታዎቂያ ወይም የንግድ ፕሮሞሽን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ የንግድ ስራዎችን እንዲሰሩ ህጋዊ ፈቃድ ያለው መሆኑን የሚገልጽ የጸና ንግድ ስራ ፈቃድ እና የንግድ ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍ ኮፒ፤

ሐ) የንግድ ትርዒቱን ወይም ባዛሩን ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛሩን መጠሪያ፣ የሚካሄድበት ቦታ፣ ጊዜ፣ ዓላማ እና የሚቀርቡ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ዝርዝር በግልጽ የሚያመላክት የፈቃድ መጠየቂያ ህጋዊ ደብዳቤ፤

መ) የንግድ ትርዒቱን ወይም ባዛሩን ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛሩን ለማካሄድ በአንቀጽ 9 መሠረት ዝግጅቱ የሚካሄድበት ቦታ የተፈቀደለት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ፤

ሠ) ለንግድ ትርዒት ወይም ባዛር ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛር ዝግጅት የፈቃድ አገልግሎት ክፍያ ብር 5000.00 (አምስት ሺ ብር)፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ጥያቄ አቅራቢዎች በህግ የተቋቋሙ መንግስታዊ ተቋማት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ የሙያ ማህበራት፣ ህብረት ስራ ማህበራት፣ የንግድና ዘርፍ ምክር ቤቶች እና ኢንተርፕራይዞች ከሆኑ፣

ሀ) ተቋሙ የተቋቋመበት ህግ ወይም ደንብ ኮፒ፤

ለ) የተቋሙ ስራ አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ኮፒ፤ በውክልና ከሆነ የተወካዩ የውክልና ማስረጃና የታደሰ መታዎቂያ፤

ሐ) የተሳታፊዎች ህጋዊ የስራ ፈቃድ እና መመስረቻ ጽሁፍ ኮፒ፤

መ) የንግድ ትርዒቱን ወይም ባዛሩን ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛሩን መጠሪያ፣ የሚካሄድበት ቦታ፣ ጊዜ፣ ዓላማ እና የሚቀርቡ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ዝርዝር በግልጽ የሚያመላክት ስልጣን ባለው ኃላፊ የቀረበ የፈቃድ መጠየቂያ ህጋዊ ደብዳቤ፤

ሠ) የንግድ ትርዒቱን ወይም ባዛሩን ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛሩን ለማካሄድ በአንቀጽ 9 መሠረት ዝግጅቱ የሚካሄድበት ቦታ የተፈቀደለት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ፤

ረ) ለአንድ የንግድ ትርዒት ወይም ባዛር ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛር ዝግጅት የፈቃድ አገልግሎት ክፍያ ብር 5000.00 (አምስት ሺ ብር)፤

## 8. በፈቃድ ማመልከቻ ላይ ውሳኔ ስለመስጠት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10.9 መሠረት ፈቃድ ጠያቂው በወቅቱ ሪፖርት ካላቀረበ እንዲሁም በክትትልና ቁጥጥር ሂደት የቀረበውን ሪፖርት ወይም መረጃ ችግር ያለበት ሆኖ ከተገኘ የተጠየቀው ፈቃድ አይሠጥም፡፡

2. ቢሮው የፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ቀድሞ ለወሰደው ፈቃድ በትክክል ሪፖርት ማቅረቡ ተረጋግጦ እና በክትትልና ቁጥጥር ወቅት ችግር የሌለበት መሆኑ ሲረጋገጥ በአገልግሎት መስጫ ስታንዳርዱ መሠረት ለአመልካቹ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

3. ቢሮው ጥያቄውን ያልተቀበለ ከሆነ በተቀመጠው የስረታንዳርድ ጊዜ ውስጥ ያልተቀበለበትን ምክንያት በጽሁፍ ለአመልካቹ ይሰጣል፡፡

## 9. የቦታ እና የፈቃድ የቆይታ ጊዜ

1. በኤግዚቢሽን ማእከል እና የገበያ ልማት ድርጅት ከሚካሄድ ዝግጅት ውጭ በዚህ መመሪያ መሠረት ለንግድ ትርዒት፣ ባዛር፣ የንግድ ትርዒትና ባዛር በተፈቀደ ባዶ ቦታ ወይም አዳራሽ ወይም አጥር ግቢ የሚፈቀደው ይዞታውን የሚያስተዳድረው አካል ሲፈቅድ ከ10 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ብቻ ነው፡፡
2. በአደባባይ እና በመንገድ ዳርቻ የሚካሄድ ከሆነ አደባባዩን ወይም መንገዱን የሚያስተዳድረው የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ለቢሮው የሚጽፈውን ደብዳቤ መሠረት በማድረግ እስከ ሰባት ቀናት ብቻ ነው፡፡

# ክፍል ሶስት

## 10. የአዘጋጁ ግዴታ

ማንኛውም የንግድ ትርዒት፣ ባዛር ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛር አዘጋጅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግዴታዎች ይኖርበታል፡፡

1. ከቢሮው የንግድ ትርዒት፣ ባዛር ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛር ፈቃድ ማውጣት አለበት፤
2. የንግድ ትርዒት፣ ባዛር ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛር ለማዘጋጀት የሚቀርብ የፈቃድ ጥያቄ ዝግጅቱ ከመካሄዱ ከ7/ሰባት/የሥራ ቀናት በፊት መቅረብ አለበት፤
3. በንግድ ትርዒት፣ ባዛር ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛር ላይ የሚሳተፉ አካላት የጸና የንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸው መሆን አለባቸው፤
4. የንግድ ትርዒቱን፣ ባዛሩን ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛሩን ከተፈቀደለት ቀን በላይ እና ከተፈቀደለት ቦታ ውጭ ያለማካሄድ፤
5. በንግድ ትርዒቱ፣ ባዛሩ ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛሩ የሚያቀርቧቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ከውጭ ሀገር የሚገቡ ከሆነ ቀደም ብለው ተገቢውን የጉምሩክ ፎርማሊቲ ወይም አሰራሮችን መከናውን አለባቸው፣

6. ተሳታፊዎች የሚያቀርቧቸው ምርቶችና አገልግሎቶች የፈጠራ ውጤቶች በሚሆንበት ጊዜ ከሚመለከተው አካል የተሰጠው የአእምሯዊ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

7. በሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚያቀርቧቸው ምርቶችና አገልግሎቶች በህብረተሰቡና በአካባቢው ደህንነትና የባህል ወይም ሌላ አሉታዊ ተጽኖ የማያስከትሉ እና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆን አለባቸው፤

8. ተሳታፊው ምርቶቹን ወይም አገልግሎቶቹን በሀገር ውስጥ እንዲሸጥ ፈቃድ የተሰጠው ከሆነና ግብይቱን በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በወጣ ደረሰኝ የማካሄድ ግዴታ ካለበት እያንዳንዱን ግብይት ማሽኑ ካልተበላሸ በስተቀር ከሽያጭ መመዝገቢያ በወጣ ደረሰኝ ማከናወን ይኖርበታል፡፡

9. የንግድ ትርዒት፣ ባዛር ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛሩን ከፈጸሙ በኋላ ዝግጅቱ በታሰበለት ዓላማ መካሄዱን፤ የተሳታፊ ድርጅቶች ብዛት፤ ከተለያዩ አካላት የተደረገን ድጋፍና ያጋጠሙ ችግሮች ተለይተው በ7 ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ለሰጠው አካል ዝርዝር የአፈጻጸም ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

10. በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ በህብረት ሥራ ማህበራት የሚቀርቡ ምርቶች እና አገልግሎቶች ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ፤

11. ዝግጅቱ በሚካሄድበት ቦታ እና ቀናት የአካባቢውን ንፅህና መጠበቅ ፤ ሰላምና፣ ፀጥታ ያለማወክ፣

## 11. ስለተቆጣጣሪ

1. እንደ አግባቡ ቢሮው፣ ተቆጣጣሪዎች ይመድባል፤
2. ተቆጣጣሪዎች ወደ ንግድ ትርዒት፣ ባዛር ወይም የንግድ ትርዒትና ባዛር የሚካሄድባቸው ቦታዎች ለቁጥጥር ተግባር ሲሄዱ ማንነታቸውን የሚገልጽ መታወቂያ ማሳየት አለባቸው፤
3. ተቆጣጣሪዎች ለቁጥጥር ሥራ ላሰማራቸው የስራ ኃላፊ ከስራ መልስ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው፤

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 12. አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ

ቢሮው ይህን መመሪያ ተላልፎ በሚገኝ ማንኛውም ሠው ላይ ከዚህ በታች በተመለከተው መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

1. ፈቃድ ሳይኖረው በንግድ ትርዒትና ባዛር ስራ ላይ ተሰማርቶ ሲያገኝ ስራውን ያግዳል፣ ያሽጋል፣ ያለፈቃድ በመስራት ክስ ይመሰረታል፣
2. ከተፈቀደው አላማ ውጪ ሌላ ተግባር ሲካሄድ ካገኘ ስራውን ያግዳል፣ የሰጠውን ፈቃድ ይሠርዛል ከተፈቀደው ውጪ በመስራቱ ክስ ይመሰርታል፣
3. ከተፈቀደው ቀን ወይም ቦታ ውጪ ሲያካሂድ ከተገኘ ስራውን እንዲያቆም ይደረጋል፣ ከተፈቀደው ቀን ወይም ቦታ ውጪ በመስራቱ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣
4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 9 መሠረት ዝግጅቱን ካጠናቀቀ በኋላ ሪፖርት ካላቀረበ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

## 13. በአስተዳደራዊ እርምጃ ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ

1. ቢሮው በሚወስዳቸው ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ቅሬታውን ለቢሮው ኃላፊ በሰባት ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የቢሮው ኃላፊ ለቀረበው አቤቱታ በሶስት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለአመልካቹ መስጠት አለበት፡፡

## 14. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ በቢሮው ሊሻሻል ይችላል፣

## 15. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በቢሮው እና በራሱ በፍትሕ ሚኒስቴር ድረ-ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በቢሮው እና በራሱ በፍትሕ ሚኒስቴር ድረ-ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ቢኒያም ምክሩ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ኃላፊ

መጋቢት 16 ቀን 2016ዓ.ም